DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# Out-of-Boundary K-12 Lottery School Year 2012-2013

ከመኖሪያ ክልል ውጪ የምዝገባ ዕጣ፣ ወላጆች፣ ልጃቸው ከተመደበበት ትምህርት ቤት (ቤቶች) ውጪ፣ ሊገኙ በሚችሉ ክፍት ቦታዎች ማመልከት እንዲችሉ በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚሰጥ አገልግሎት ነው። የልጅዎን ምድብ ትምህርት ቤት (ቤቶች) ለማወቅ፣ እባክዎን dcatlas.dcgis.dc.gov/schools ን ይቃኙ። ይህ የሎተሪ ዕጣ፣ አሁን ባሉበት ትም ህርት ቤት፣ እንደ ከመኖሪያ ክልል ውጪ (ከዚህ በታች በተራ ቁጥር #9 ላይ የሰፈረውን ይመልከቱ) እንደመጡ ሆነው ለሚማሩ ወይም ከተማ አቀፍ በሆኑ በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመመዝገብ ለሚፈልጉ ወይም ተማሪዎች (ይህን ይመልከቱ http://dcps.dc.gov/DCPS/highschoolapp) የሚውል አይደለም።

## ዋና ጉልህ ጭብጦች (Fast Facts)፤

- ለ 2012-2013 የትምህርት ዓመት፣ ከመኖሪያው ክልል ውጪ የማመልከቻው ወቅት ጥር (**January) 30, 2012 ይጀመር** እና **የካቲት** (**February) 27, 2012**.** **ያበቃል።**

  እባክዎን ዕጣው ከመጀመሩ አንድ ሣምንት በፊት በትክክል ስለሚጀመርበት እና ስለሚያበቃበት ሰዓት ለማወቅ dcps.dc.gov ን ይቃኙ።
- እያንዳንዱ አመልካች፣ ከመኖሪያ ክልል ውጪ በሆኑ እስከ ስድስት በሚደረሱ የትምህርት ፕሮግራሞች ማመልከት ይችለል።
- የሎተሪ ዕጣ የማመልከቱ ተግባር በኢንተርኔት አማካይነት መጠናቀቅ የሚርበት ሲሆን፣ ከዚህ ውጪ በወረቀት የሚደረግ ማመልከት ተቀባይነት አይኖረውም።
- የዕጣው ውጤት መጋቢት (March) 2  በኢንተርኔት አማካይነት ይገለጽ እና፣ መጋቢት (March) 9 ቀን በፖስታ ቤት በኩል በየቤቱ ይላካል።
- በሎተሪው፣ ቦታ የማግኘት ዕድል የወጣላቸው አመልካቾች ዕድሉን ለመቀበል “Letter of Intent to Accept Lottery Seat” (“የሎተሪ ዕጣው ያስገኘውን ቦታ ለመቀበል የመ ፈለግ አዝማሚያ መግለጫ ደብዳቤ”) ቅጽ፣ ሚያዚያ (April) 2 ቀን (የነዋሪነት ማረጋገጫ ወረቀት ጭምር) በመላክ ዕጣውን መቀበላቸውን መግለጽ አለባቸው። አመልካቾች በተጨማሪ ተሞልቶ የተጠናቀቀውን ሙሉ የመመዝገቢያ ማመልካቻ፣ ዕጣው ያስገኘውን ቦታ እንዲጠበቅ ለማድረግ ግንቦት (May) 2 ቀን (የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫው ጭምር) ገቢ መደረግ አለበት። በዚህ ጊዜ በትምህርት ቤቱ ክልል ነዋሪ መሆንን እና የወንድም የእህት በዚያ ትምህርት ቤት የመማር ምርጫ ማረጋገጫውን ጭምር ለማቅረብ ዝግጁ መሆን አለብዎት።

## 1. በምዝገበው ወቅት ቀደሞ ብዬ ባመለከት፣ የተሻለ የመቀበል እድል ይኖረኛል ወይ?

የለም፣ አያገኙም። በጥር (January) 30 እና በየካቲት (February) 27፣ ባለው ጊዜ መካከል እስከ አመለከቱ ድረስ ቀደም ብሎ ማመልከቱ የሚያስገኘው የተሻለ እድል አይኖርም።

## 2. በማመለክትበት ት/ቤት ልጄ ወንድም እህት ካለው፣ ወይም በትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ክልል የሚኖር ከሆነ፣ የተሻለ የመቀበል እድል ይኖረኛል ወይ?

አዎን፣ ያገኛሉ። የዲሲ ማዘጋጃ ቤት ደንብ (DCMR) ልጅዎ፣ ዕጣው በወጣለት በዚያ ትምህርት ቤት ወንድም፣ ወይም እህት ካለው፣ ወይም ልጅዎ ዕጣው ወደ ወጣለት ትምህርት ቤት የሚያደርገው መመላለስ ለእግር ጉዞ አመቺነት ያለው ሆኖ የሚገኝ ከሆነ በዕጣው የቀዳሚነት እድል እንዲሰጥ ይፈቅዳል።* ልጅዎ "በወንድም እህት አማራጭ ምርጫ" በዚያ ትምህርት ቤት የመግባት እድል የሚያገኝ ከሆነ፣ ልጅዎን በትምህርት ቤቱ በሚያስመዘግቡበት ጊዜ በዚያ ትምህርት ቤት በመማር ላይ የሚገኙ ልጆችዎ ለዚህ አሁን ለሚያስመዘግቡት ልጅዎ ወንድም እህት መሆናቸውን ለማረጋገጥ ዝግጁ ሆነው መገኘት አለብዎት።

## 3. የሎተሪው ዕጣው ተግባራዊ የሚሆነው እንዴት ነው?

- የማመልከቱ ጊዜ በየካቲት (February) 27 ከበቃ በኋላ፣ እያንዳንዱ አመልካች ላመለከተበት ወይም ላመለከተችበት ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት እንደተገኘ በነሲብ በተወሰደ ቁጥር አማካይነት እንዲመደብ/እንድትመደብ ይደረጋል።
- በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት፣ ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ እንደተገኘ በነሲብ እንዲመረጥ ይደረጋል።
- በአመልካቾች የምርጫ ፍላጎት ደረጃ እና እንደተገኘ በተሰጠ የቁጥር ቅደም ተከተል አማካይነት፣ አመልካቾች ቦታ በተገኘበት በክፍል ደረጃቸው መጠን  በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት እንዲመደቡ ይደረጋል። የሚከተለው ከመኖሪያ ክልል ውጪ ከ K-12 የሎተሪ ዕጣ የአመራረጥ ቅደም ተከተል ምርጫን ያመለክታል።
  1. በነሲብ እንደተገኘ በተሰጠ ቁጥር አማካይነት፣ በዚህ ትምህርት ቤት ወንድም፣ እህት ያላቸው ተማሪዎች በመጀመሪያ ይመደባሉ፤
  2. ዕጣው በሚወጣበት ጊዜ በመዘጋት ላይ በሚገኝ ትምህርት ቤት በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች፣ በነሲብ እንደተገኘ በተወሰደ ቁጥር አማካይነት እንዲመደቡ ይደረጋል።
  3. ከትምህርት ቤቱ ለእግር ጉዞ አመቺነት ባለው ርቀት ላይ የሚኖሩ ተማሪዎች በነሲብ በተሰጡ የቁጥር ቅደም ተከተል አማካይነት እንዲመድቡ ይደረጋል*
  4. ከዚህ በላይ ከተመለከቱት የተረፉ ማናቸውም ክፍት ቦታዎች፣ በዚያ ትምህርት ቤት ወንድም እህት የሌላቸው ወይም ለትምህርት ቤቱ የመኖሪ ቤት የቅርበት አማራጭ እድል  ለሌላቸው ተማሪዎች በነሲብ በተወሰደ የቁጥር ቅደም ተከተል አማካይነት ለሌሎች ተማሪዎች ይደለደላሉ።
- ከአንድ ትምህርት ቤት በላይ በሆኑ ትምህርት ቤቶች የተመደቡ ተማሪዎች፣ በአንደኛ ደረጃነት ባስቀመጡት ትምህርት ቤት፣ ቦታ የሚያዝላቸው ሲሆን፣ ቦታ ያልተሰጣቸው ተማ ሪዎች በሙሉ በማመልከቻዎቻቸው ላይ በክፍተኛ ቅደም ተከተል ወደ አስቀመጧቸው ሌሎች የመጠባበቂያ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር ውስጥ ይያዛሉ።
- በአንድ ትምህርት ቤት የተወሰነ ክፍል ሁሉ ተይዞ ከበቃ በኋላ ተቀባይነት ሳያገኙ የቀሩ ተማሪዎች ከላይ በተገለጸው መሠረት የምርጫ መጠባበቂያ ዝርዝር ውስጥ እንዲያዙ  ለማ ድረግ የመጠባበቂያ ዝርዝር ተዘጋጅቶ ይቀመጣል።

## 4. ምርጫዎቼን በቅደም ተከተል የማስቀምጥበት ሁኔታ፣ የሎተሪ ዕጣዬ ውጤት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል ወይ?

አዎን። በሎተሪው ዕጣ ወቅት፣ እንድ ተማሪ ከአንድ ትምህርት ቤት በላይ የተመደበ ከሆነ፣ እሱ/እሷ በከፍተኛ ሁኔታ በአንደኛ ደረጃ ምርጫ ላይ ባስቀመጠው/ጠችው  ትምህርት ቤት፣ ቦታ ይሰጠው/ጣት እና በማመልከቻው ላይ ሰፍረው የቀረቡ ሌሎች ትምህርት ቤቶች ሁሉ በመጠበቂያ ዝርዝር ውስጥ ተይዘው እንዲቀመጡ ይደረጋል።

**ዲሲ የማዘጋጃ ቤት ደንብ፣ B 2106.3 “ለእግር ጉዞ አመቺነት ያለው ርቀት” የተሰኘውን አባባል የሰሜንና ደቡብ አቅጣጫዎችን በማማተር እና ትምህርት ቤትን መሀከል በማስቀመጥ፣ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ከትምህርት ማዕከላት 3000 ጫማዎች የስፋት ክልል ያልራቀ፣ እንዲሁም ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ 5000 ጫማዎች ስፋት የማይበልጠውን ሀሳባዊ ስፍራ የሚሸፍን መሆኑን ወስኖ አስቀምጧል።
**ወላጆችን በተሻለ ለመርዳት በሚደረግ ጥረት፣ የዕጣው መውጫ ቀናት ወደ ጥር የመጨረሻው ሰኞ ቀን  (last Monday in January) እንዲወጣ እንዲሁም  በየካቲት የመጨረሻው ሰኞ ቀን ( last Monday in February) እንዲያበቃ ተለውጧል።

**5. ልጄ ከአንድ ትምህርት ቤት በላይ ቦታ ማግኘት ይችላል ወይ? በአንድ ትምህርት ቤት ተቀብሎን ከገባን ለሌላ (ለሌሎች) ትምህርት ቤት (ቤቶች) ያቀረብነው ወይም ያቀረብናቸው ማመልከቻዎች ምን ይሆናሉ?**
አመልካቾች ባመለከቱባቸው ትምህርት ቤቶች ተቀባይነት የሚያገኙትን የአመልካቾች ቁጥር ከፍ ለማድረግ፣ ከመኖሪያ ክልል ውጪ የሎተሪ ዕጣ መሠረት፣ ተማሪዎች ከአንድ ትምህርት ቤት በላይ ቦታ እንዲሰጣቸው አይደረግም። ሆኖም በተራ ቁጥር 3 ላይ በተመለከተው መሠረት፣ አመልካቾች ሁሉ፣ በሎተሪው ዕጣ ወቅት ተቀባይነት ባላገኙበት በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በመጠባበቂያ ዝርዝር ውስጥ ተመዝግበው ይያዛሉ።

**6. የተወሰነ ክፍል ለመግባት የማመለክትበት ትምህርት ቤት፣ ከመኖሪያ ክልላቸው ውጪ የሚያመለክቱ ተማሪዎችን የማስተናግድበት ቦታ ሊኖረኝ አይችልም ብሎ በሚገምት ትምህርት ቤት ማመልከት እችላለሁ ወይ?**
አዎን፣ ማመልከት ይችላሉ። ክፍት ቦታ ምናልባት ቆይቶ ሊገኝ የሚችል ሆኖ ከተገኘ፣ ልጅዎ በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ እንዲያዝ ይደረጋል።

**7. በአንድ በተወሰነ ትምህርት ቤት ክፍት ቦታዎች መኖራቸውን ማወቅ የምችለው እንዴት ነው? በትምህርት ቤቱ የሚኖሩ ክፍት ቦታዎችስ የሚወሰኑት እንዴት ነው?**
የሚያመለክቱበትን ትምህርት ቤት እና የሚያመለክቱበትን የክፍል ደረጃ በሚመርጡበት ጊዜ፣ ማመልከቻው፣ በ 2012-2013 የትምህርት ዓመት፣ ትምህርት ቤቱ፣ ከመኖሪያ ክልል ውጪ ለሆኑ ተማሪዎች ማቅረብ እችላለሁ ብሎ የሚያስበውን የተወሰኑ ክፍሎች ቁጥር ብዛት ያመለክታል። በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ለእያንዳንዱ ክፍል ከመኖሪያ ክልላቸው ውጪ ለሚመጡ ተማሪዎች፣ ሊኖሩ የሚችሉ የቦታዎች ብዛት ቁጥር የሚወስነው፣ ለመጭው የትምህርት ዓመት፣ ከትምህርት ቤቱ ርእሠ መምህር በሚገኝ መረጃ መሠረት ላስተናግድ እችላለሁ ብሎ በሚይዛቸው የተማሪዎች ብዛት እና የትምህርት ቤቱም ሕንጻ ሊይዝ በሚችለው ክፍሎች መጠን ላይ በመመርኮዝ ነው።

**8. ከአንድ በላይ ለሆኑ ልጆቼ፣ ከመኖሪያዬ ክልል ውጪ የሎተሪ ዕጣ እና/ወይም ለቅድመ ትምህርት (Pre- school) እንዲሁም ለቅድመ k (Pre-k) ሎተሪ ዕጣዎች ባስገባ እና እነዚህም ልጆች በዚያው በአንድ ትምህርት ቤት ተመዝግበው እንዲማሩ እፈልጋለሁ። ይህ ይቻላል ወይ?**
የእያንዳንዱ ልጅ ማመልከቻ፣ በቅድመ ትምህርት/ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (Preschool/Pre-k) እና ከክልል ውጪ የሎተሪ ዕጣዎች የሚስተናገዱት ለየቅል ነው። ሆኖም አንድ ወንድም ወይም እህት በአንድ በተወሰነ ትምህርት ቤት እንዲገባ/እንድትገባ ከተደረገ፣ ሌላው ልጅ እዚያው ትምህርት ቤት ገብቶ የሚማር ወይም የምትማር ለመሆኑ ዋስትና አይኖርም። ይሁን እንጂ በሎተሪ ዕጣው አማካይነት አንድ ልጅ አንድ የተወሰነ ትምህርት ቤት የሚቀበለው ከሆነ ወንድም፣ እህቱ (ሞቹ/ቶች) ለዚህ ትምህርት ቤት (በአሁኑ ወቅት በዚያው በአንዱ ትምህርት ቤት ተመዝግበው ከሚገኙ ወንድም እህት ተማሪዎች ቀጥሎ) በከፍተኛ ደረጃ የመመዝገብ ቅድሚያ የመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ እንዲያዝ ያደረጋል።

**9. ልጄ በአሁኑ ወቅት በሚማርበት ትምህርት ቤት ከክልል ውጪ የመጣ/ች ተማሪ ሆኖ/ሆና በመማር ላይ ይገኛል/ትገኛለች። ለቀጣዩ የትምህርት ዓመት በዚያው እንዲቀጥል/ድትቀጥል ለማድረግ እንደገና በድጋሜ ማመልከት አለብኝ ወይ? ወይም፣ ለሚመጣው ዓመት እሱ/እሷ ወደ መካከለኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያልፍ ወይም የምታልፍ ከሆነ መጋቢ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ሁኔታ መሠረት "በምድብ ትምህርት ቤት" ቦታዬን ለመጠበቅ ከክልል ውጪ አማካይነት ማመልከት ያስፈልገኛል ወይ?**
የለም፣ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ ተማሪዎች በትምህርት ዘመናቸው የማያቋርጥ ጽኑ የሆነ ጎዳና ይዘው እንዲጓዙ የሚያስችላቸው ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው ይፈልጋል። ስለሆነም፣ በአንድ ትምህርት ቤት ከመኖሪያ ክልላቸው ውጪ የተመዘገቡ ተማሪዎች፣ በትምህርት ቤቱ ሊኖሩ የሚችሉ የክፍል ደረጃዎችን እስኪጨርሱ ድረስ በዚያው ትምህርት ቤት ቆይተው ትምህርቶቻቸውን የማጠናቀቅ እና እንዲሁም እንደ መጋቢነቱ ይዞታ የትምህርት ቤቱ ተቀባይ ወደ ሆነው ቀጣዩ ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርታቸውን የመቀጠል መብት አላቸው። የትምህርት ቤትዎን ቀጣይ ትምህርት ቤት የሆነውን ትምህርት ቤት ለማወቅ፣ እባክዎን profiles.dcps.dc.gov. ይቃኙ።

**10. አራት ዓመት የሞላውን ልጄን በመዋዕለ ሕጻናት(kindergarten) ላስገባው እፈልጋለሁ። ይህ ይፈቀዳል?**
የለም፣ አይፈቀድም። የዲሲ ማዘጋጃ ቤት ደንብ፣ መዋዕለ ሕጻናት (kindergarten) ለመግባት የሚፈልጉ ተማሪዎች በመስከረም (September) 30, 2012 አምስት ዓመት የሞላ ቸው መሆን እንዳለባቸው ያመለክታል። ከቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (pre-kindergarten) እስከ ቅድመ ትምህርት (Preschool) እና ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (pre-kindergar-ten) የሎተሪ ዕጣ ቦታ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ።

**11. ላመለክትበት (ባቸው) ስለምፈልገው ወይም ስለምፈልግባቸው ትምህርት ቤት/ቤቶች የበለጠ ማወቅ የምችለው እንዴት ነው?**
ስለ ዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች፣ ስለ ትምህርት ቤት ገጽታዎች፣ ለሕዝብ ለመታየት ክፍት ስለሆኑ (Open Houses) ትምህርት ቤቶች በወቅቱ ስላለው ሁኔታ፣ ከመኖሪያ ክልል ውጪ የሎተሪ ዕጣ አወጣጥ ሂደት ፖሊሲዎችን ጭምሮ የበለጠ መረጃዎች ለማግኘት profiles.dcps.dc.gov ን ይቃኙ።

**12. ልጄ የሚከተለው የግል የትምህርት እቅድ (IEP) ካለው ለሎተሪው ዕጣ ላመለክት እችላለሁ ወይ?**
አዎን፣ ለልጅዎ የሚሰጠውን ልዩ የትምህርት ፕሮግራም በተመለከተ የተወሰኑ ጥያቄዎች ካለዎት እባክዎን 202-442-5400 ይደውሉ።

**13. ልዩ ትምህርት ለሚሰጡ ልዩ (specialized) ከተማ አቀፍ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የማመለከተው እንዴት ነው?**
ለ 2012-2013 የትምህርት ዓመት ልዩ ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች ገብቶ ለመማር የሚፈልጉ ተማሪዎች፣ በተለመደው ማመልከቻ መጠቀም አለባቸው። ለበለጠ መረጃ እባክዎን ድረ ገጻችን የሆነውን http://dcps.dc.gov/DCPS/highschoolapp. ይቃኙ።

**14. ኢንተርኔት ከሌለኝ ማመልከቻውን አጠናቅቄ በመሙላት ገቢ ማድረግ የምችለው እንዴት ነው?**
የኢንተርኔት አገልግሎት የሌለዎት ከሆነ ፣ ማመልከቻውን ሞልተው የሚልኩባቸው በርካታ መንገዶች አሉ።

- በነጻ በኢንተርኔት ለመጠቀም በክልልዎ የሚገኝ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ቤትን ይጎብኙ።
- በአጎራባችዎ ወደሚገኝ የዲሲፒኤስ የሕዝብ ትምህርት ቤት ጎራ ይበሉ። የትምህርት ቤቱ እንግዶች የመቀበያ እና ማስተናገጃ ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች በትምህርት ቤቱ ኮምፒዩተር ማመልከቻውን እንዲሞሉ ይረዱዎታል።
- ለ Critical Response ቡድናች በ 202-478-5738 ይደውሉ። የ Critical Response ቡድኑ፣ ማመልከቻ ሞልተው እንዲያስረክቡ በስልክ ለመርዳት ደስተኞች ናቸው።

*ማስታወሻ፤: ለ 2 ክፍል እና ከዚያም በላይ ላሉ ክፍሎች፣ በ ከክልል ውጪ ዕጣ (Out-of-Boundary Lottery) ዕጣ አማካይነት ለመንታ የቋንቋ ( dual-language program) ፕሮግራም ለክፍላቸው ተመጣጣኝ የሆነ (grade-appropriate Spanish language skill) የስፓኒሽ ቋንቋ ክህሎት ማሳየት መቻል አለባቸው።*

*Eastern ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ለ 2012-2013 የትምህርት ዓመት የ 9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ይቀበላል።*